## ደንብ ቁጥር 167/2016

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ (ማሻሻያ) ደንብ

በከተማው ውስጥ የለሙ ፓርኮች፣ ኮሪደሮች፣ መንገዶችና ተጓዳኝ ልማቶች ካላቸው ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ከባቢያዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ለከተማችን ጽዳት፣ ውበትና መልካም ገጽታ የላቀ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆኑ ጽዳታቸውን፣ ውበታቸውንና መልካም ገጽታቸውን የሚያበላሹ ተግባራትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ሥራ ላይ የቆየውን የደንብ ማስከበር ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 95 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 150/2015 (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር 167/2016» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "**ደንብ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 150/2015 ነው፡፡
   2. በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት ወይም ሐረጎች የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ባወጣቸው አግባብ ባላቸው ደንቦች ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደአግባብነቱ ለዚህ ደንብም ያገለግላሉ፡፡

3. <u>ማሻሻያ</u>

1. የደንቡ አንቀጽ 15፣ 16፣ 17 እና 18 ተሰርዘው በአዲስ አንቀጽ 15፣ 16፣ 17 እና 18 ተተክተዋል፤

"15. <u>ስለአስተዳደረዊ እርምጃ አወሳሰድ</u>

1. በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው የወንጀል ወይም የደንብ መተላለፍ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውንም ሰው ላይ፡-

   ሀ) እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቀም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የግንባታ ፈቃድ እንዲሰረዝ የማድረግ፣ የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ ስልጣን ላላቸው ተቋማት በጽሑፍ የማሳወቅ እና የገንዘብ ቅጣት የመክፈል አቅም የሌላቸው መሆኑ በጽሕፈት ቤቱ የተረጋገጠላቸውን ተቀጪዎች አካባቢውን የማጸዳት ወይም አቅምን ያገናዘበ አካላዊ እንቅስቃሴ የማሰራት እርምጃ ይወስዳል፤

   ለ) ከደንቡና ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

2. በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ደንብ የተላለፈ ሰው በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት የወረዳው ጽህፈት ቤት ቀርቦ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቱን ገቢ ማድረግ እና የተጣለበትን ሌላ ቅጣት መፈጸም አለበት፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የደንብ መተላለፍ የፈጸመው ሰው የገንዘብ ቅጣት የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ደንብ ተላላፊው አካባቢውን ያጸዳል ወይም አቅሙን ያገናዘበ አካላዊ እንቅስቃሴ ይሰራል ወይም ሌላ የጉልበት ሥራ ይሰራል፤

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ መተላለፍ በተፈጸመበት ቦታ ቋሚ አድራሻ የሌላቸው ደንብ ተላላፊዎችን በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የቅጣት

ገንዘቡን ከፖሊስ ጋር በመሆን እንዲከፍሉ ያደርጋል፤

lawyer.et
When Results Count.

5. የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤
7. እንደጥፋቱ ክብደት እና እንደፈጻሚው ግንዛቤ ደረጃ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ደንብ ተላላፊው የፈጸመውን ጥፋት እና የተወሰነበትን አስተዳደራዊ ቅጣት በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፤
8. ባለሥልጣኑ በደንቡ እና በዚህ ደንብ የተደነገጉ ጥፋቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በተለያየ ዘዴ የማደራጀት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፤
9. ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዘን ወይም እየተያዘ ያለን የመንግስት መሬት ያስለቅቃል፤ ያለግንባታ ፈቃድ የተገነባን ወይም እየተገነባ ያለን ግንበታ ያፈርሳል፤
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት መቀጮውን ገቢ ለማድረግ ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በቅጣት ሰንጠረዥ የተቀመጠውን የመቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል እና እስከ ሰሶት ወር የሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት እንዲቀጣ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል፡፡

**16.** <u>ስለተደጋጋሚ ጥፋትና አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

ማንኛውም ደንብ ተላላፊ የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ የፈፀመ እንደሆነ፡-

1. በመጀመሪያ ደንብ መተላለፍ በቅጣት ሰንጠረዥ የተገለጸውን አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ እጥፍ ይከፍላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   ሀ) የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰረዛል፤ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣
   ለ) የግንባታ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የግንባታ ፈቃዱ ይሰረዛል፤ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፤
   ሐ) አሽከርካሪ ከሆነ የመንጃ ፈቃዱ ይሰረዛል፤

መ) መኖሪያ ቤት ከሆነ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፤

ሠ) መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሆነ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ክፍያውን ካልፈጸመ ወይም ግዴታውን ካልተወጣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ክፍያውን እንዲከፍል ወይም ግዴታውን እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

**17. ቅጣትን ስለማስፈፀም**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተወሰነውን አስተዳደሪዊ የገንዘብ ቅጣት እና የተጣለበትን ሌላ አስተዳደራዊ ቅጣት በተመለከተ፡-

ሀ) አስተዳደሪዊ የገንዘብ ቅጣቱን በወረዳው ጽሕፈት ቤት ያስፈጽማል፤

ለ) አካባቢውን እንዲያጸዳ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ወይም ሌላ የጉልበት ሥራ እንዲሰራ የተወሰነበትን ደንብ ተላላፊ የደንብ ጥሰቱ የተፈጸመበት ቦታ ላይ ያስፈጽማል፤ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ከባለሥልጣኑ የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብለት ይተባበራል፤

2. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገጉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ለደንብ ተላላፊው ፈቃድ ለሰጡ ወይም አገልግሎት ለሚያቀርቡ አስፈጻሚ ተቋማት ውሳኔውን በመላክ እንዲፈጸም ያደርጋል፤

3. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት የተወሰነው አስተዳደራዊ ቅጣት ተፈጻሚ እንዲሆን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ይልካል፤ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

4. ከባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲያስፈጽሙ ውሳኔ የተላከላቸው አስፈጻሚ ተቋማት ቅጣቱን ያስፈጽማሉ፤

5. የወረዳው ጽህፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገውን ወይም ያልፈጸመውን ማንኛውም ደንብ ተላላፊ በደንቡ ላይ የተገለጸው አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲፈጽም ለሚመለከተው አካል ክስ እንዲመሰረትበት ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ክስ እንዲመሠረት የተደረገበት ደንብ ተላላፊ እንደአግባቡ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

18 ስለአቤቱታ አቀራረብ

1. ይህንን ደንብ በመተላለፉ በተሰጠው ቅጣት ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም የውሃ አቅርቦት የተቋረጠበት ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለወረዳው ጽህፈት ቤት ለማቅረብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ቅሬታ የተቀበለ የወረዳ ጽህፈት ቤት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ይወስናል፤ ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ያሳውቃል፤
3. ቅሬታ አቅራቢው ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ካገኘና አስተዳደራዊ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል በቂ ምክንያት ካለው የወረዳው ጽህፈት ቤት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በመሻር ፈቃዱን ለሰረዘው ወይም አገልግሎቱን ላቋረጠው አስፈጻሚ ተቋም ፈቃዱ እንዲመለስ ወይም የተቋረጠው የውሃ አቅርቦት እንዲቀጠል ይደረጋል፤
4. ይህንን ደንብ በመተላለፍ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው መክፈል ከሚገባው የመጨረሻው ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት የስራ ቀናት ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ ጽህፈት ቤት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፤
5. የወረዳ ጽህፈት ቤት የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ በ5 (በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይወስናል፤ ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ያሳውቃል፤"

2. የደንቡ የቅጣት ሰንጠረዥ 2 ተሰርዞ በሚከተለው የቅጣት ሰንጠረዥ 2 ተትከቷል፤

"የቅጣት ሰንጠረዥ 2

በሕገወጥ መንገድ ፍሳሽም ሆነ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንኛውም ሰው ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በግቢው ውስጥ በአግባቡ አለመያዝ፤ በዓይነት አለመለየት፤ ማዝረክረክ፤ ለጤናና የአካባቢ ገጽታ በሚጎዳ መልኩ ማከማቸት፤<br>ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>ከድርጅት ከሆነ | ብር 2000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ደረቅ ቆሻሻ ማንሳት |
| 2 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት/ማህበር<br>ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ በአካባቢው ላይ ካንጠባጠበ ወይም የአካባቢውን ገጽታ ካበላሸ<br>በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኛው ተገቢውን አገልግሎት ካልሰጠ<br>ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እውቅና ውጭ የአገልግሎት ክፍያ ከደንበኛው ከተቀበለ<br>ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቦታዎችን እስከ 5 ሜትር ዙሪያ ድረስ ጽዱ ካላደረገ | ብር 25000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 3 | ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ እውቅና ሳይኖረው በግል፤ በማህበርም ይሁን በድርጅት ስም በግቢ ውስጥ ወይም በክፍት ቦታ ላይ ያከማቸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማስወገድ |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 4 | በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ የተሰማራ ግለሰብ፤ ማህበር ወይም ድርጅት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት የዋለ ደረቅ ቆሻሻ መረጃ ለሚጠይቀው ህጋዊ አካል ካልሰጠ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና መረጃ መስጠት |
| 5 | በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ የለቀመ ወይም ያከማቸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 6 | ደረቅ ቆሻሻን ከግቢው አውጥቶ ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም ያስቀመጠ ማንኛውም ሰው፤<br>የመኖሪያ ቤት ቆሻሻ ከሆነ<br>የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ከሆነ<br>የጤና ተቋም ቆሻሻ ከሆነ<br>ከሌሎች ድርጅቶች የመነጨ ቆሻሻ ከሆነ | ብር 2000.00<br>ብር 50,000.00<br>ብር 30,000.00<br>ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 7 | ከመኪና ውስጥ የመነጨን ደረቅ ቆሻሻ በማንኛውም ባልተፈቀደ ቦታ ጠርጎ የጣለ ማንኛውም ሰው፤<br>አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ከመኪና ውስጥ ሆኖ በመስኮትም ይሁን በበር በኩል ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ወደ ውጭ የወረወረ ወይም የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 5,000.00<br>ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 8 | ማንኛውም በመንገድ የሚንቀሳቀስ ሰው የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ ፌስታል፣ የጫት ገለባ፣ የፍራፍሬ ተረፈ- ምርቶች፣ የትራንስፖርት ቲኬት፣ የሞባይል ካርዶችን፣ የማስቲካና ከረሜላ ሽፋኖች፣ የመሳሰሉት ጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ ወይም በፓርኮች፣ | ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በአረንጓዴ ቦታ፣ በኮሪደር | | |

lawyer.et
When Results Count.

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| | መሰረተ ልማቶች፣ በመናፈሻ ቦታ፣ በክፍት የሕዝብ መናፈሻ፣ በመንገድ መናፈሻ፣ በመንገድ፣ በመንገድ አካፋይ፣ በመንገድ ዳርቻ፣ በአደባባይ፣ በፕላዛ ቦታ የመንገድ ቱቦ፤ ድልድይ ውስጥ፤ በክፍት ቦታ በመሳሰሉት ላይ ከጣለ ወይም ከወረወረ፤ | | |
| 9 | ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው አሸዋ፣ አፈር፣ ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ የግንባታ ፍርስራሽ ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማስቀመጥ አካባቢን ካቆሸሸ፤<br><br>በመንገድ ወይም በሌላ ባልተፈቀደ ቦታ በፓርኮች፣ በአረንጓዴ ቦታ፣ በኮሪደር መሰረተ ልማቶች፣ በመናፈሻ ቦታ፣ በክፍት የሕዝብ መናፈሻ፣ በመንገድ መናፈሻ፣ በመንገድ፣ በመንገድ አካፋይ፣ በመንገድ ዳርቻ፣ በአደባባይ፣ በፕላዛ ቦታ እና በመሳሰሉት ቄጠማ፤ ሳር፤ የበቆሎ ሸፋን ወይም ቆረቆንዳ፤ ጭድ፤ ሸንኮራ አገዳ፤ የሽንብራና የባቄላ እሸት ገለባ፤ የፍራፍሬ ልጣጭ እና የመሳሰሉት ሲሸጥ አካባቢውን ያቆሸሸ ወይም ግብዓቱን ተጠቅሞ ተረፈ ምርቱን የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 25,000.00<br><br>ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 10 | አፈር፤ አሸዋ፤ ጠጠር፤ ሳርና ሌሎች ተረፈ ምርቶች በተሽከርካሪ ሲጓጓዝ በሸራ ወይም በመረብ ሳይሸፍን ወይም በአግባቡ ባለመሸፈኑ ምክንያት አካባቢውን ያቆሸሸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 10,000.00 ለግለሰብ<br>ብር 25,000.00 ለድርጅት | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

lawyer.et
When Results Count.

| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት/ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ጊዜያ ማቆያ ወይም ማስወገጃነት ከፈቀደው ቦታ ውጭ ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ ካስቀመጠ፤ ከጣለ፤ ካቃጠለ ወይም ከቀበረ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 12 | ከመፀዳጃ ቤት ውጭ በማንኛውም ቦታ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 13 | በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎችን<br><br>ያለ ህጋዊ ፈቃድ ከአካባቢው ያስወገደ፤ ነቅሎ የጣለ፤ ያበላሸ፤ የሰበረ፤ የወሰደ፤ ለሌላ አገልግሎት ያዋለ ማንኛውም ሰው፤<br><br>ማስታወቂያ የለጠፈ ወይም በላያቸው ላይ እቃ ያስቀመጠ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 50,000.00<br><br>ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንብረቱን መመለስ ወይም ማስታወቂያውን ማንሳት |
| 14 | በአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና የማምረቻ ድርጅቶች ተገቢ የሆነ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ በግቢው ውስጥና በአካባቢው አለማስቀመጥ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ደስት ቢን ማስቀመጥ |
| 15 | ከቤት እንስሳት የሚወጡ እዳሪ (ኩስ፤ ፍግ፤ እበት)፤ እና የእንስሳት የምግብ ተረፈ ምርቶችን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም አካባቢውን ያቆሸሸ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳትና አካባቢውን ማጽዳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 16 | የተለያዩ እንስሳትን ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማጸዳዳት አካባቢውን ማቆሸሽ፤ | ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻ ማንሳት |
| 17 | ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ አፈር፤ አሸዋና ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ሳይሸፍን በጋማ ከብት በማጓጓዝ አካባቢውን ያቆሸሸ ወይም ያዝረከረከ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 18 | የሞተ እንስሳን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 25000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |

When Results Count.

| | | | |
|---|---|---|---|
| 19 | በአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማዕከላትና የተለያዩ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተረፈ ምርታቸውን ደረቅ ቆሻሻ<br><br>ከንግድ ማዕከሉ ግቢ ውጭ ወይም መንገድ ዳር ተረፈ ምርት ቆሻሻ ያከማቸ ያስቀመጠና የጣለ፤<br><br>ከተሽከርካሪ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭንና ሲያወርድ የሚወዳድቁ የአትክልት ትርፍራፊ ቆሻሻ ወዲያው ያላጸዳ፤<br><br>የገበያ ማዕከሉን ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጭ ሰብስቦ ኤጀንሲው በፈቀደው ህጋዊ ማስወገጃ ቦታ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማእከላት ያላስወገደ፤<br><br>ከመደብሩ ፊት ለፊት የመደብር ጥራጊ፤ በሽያጭ ወቅት የተከሰቱ የእቃ ማሸጊያ፤ የጫት ገራባ፤ ካርቶን የመሳሰሉትን ካስቀመጠ፤ | ብር 50,000.00<br><br>ብር 5,000.00<br><br>ብር 50,000.00<br><br>ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 20 | ከግንባታ ወይም ከፍርስራሽ የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ግለሰብ/ድርጅት<br><br>በከግንባታ ማዕከል በተሽከርካሪ ጎማ እንቅስቃሴ ወይም በጭነት ወቅት በሚንጠባጠብ አፈር፤ ጭቃ፤ ፍርስራሽ የመሳሰሉትን ምክንያት በሚፈጠር ቆሻሻ አካባቢውና መንገዱ ያበላሸ የግንባታ ባለቤት | ብር 5,000.00 ለአሻከርከሪ/ **ብር** 50000.00 **ለድርጅት**<br><br>ብር 5,000.00 ለአሽከርካሪ/ **ብር** 50000.00 **ለድርጅት** | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| **ተ.ቁ** | **የጥፋት ዓይነቶች** | **የቅጣት ክፍያ መጠን** | **ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ** |
|---|---|---|---|
| 21 | የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርትን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ<br><br>ግለሰብ/<br><br>ድርጅት | ብር 5,000.00<br><br>ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |

lawyer.et
When Results Count.

| | | | |
|---|---|---|---|
| 22 | ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ተገቢነት የሌለውን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ፣ ማቃጠያ ማዕከል፣ ቅብብሎሽ ጣቢያ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከል ያጓጓዘ ድርጅት/ማህበር/ግለሰብ/ተቋም፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያመጣውን ቆሻሻ መመለስ |
| 23 | አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን በተለየ መልኩ በመለየት በአግባቡ እና አካባቢውን በማይበክል መንገድ እንዲወገድ ያላደረገ ማንኛውም ሰው፤ | ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 24 | ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት ግቢ ውጭ ያለውን የአካባቢ ንጽህና አረንጓዴ አድርጎ አለመጠበቅ፡-<br>ከመኖሪያ ቤት አጥር ግቢ ውጭ እስከ 5 ሜትር ርቀት አለማጽዳት፤<br>ከድርጅት/ተቋም አጥር ግቢ ውጭ እስከ 10 ሜትር አለማጽዳት፤ | ብር 20000.00<br>ብር 100,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 25 | ወቅታዊና ልዩ ዝግጅት አከናውኖ በዓሉ ሲጠናቀቅ በዕለቱና ወዲያው ዝግጅቱ የተከናወነበትን አካባቢ ከቆሻሻ ያላጸዳ የፕሮግራሙ አዘጋጅ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 26 | ዓመታዊ፣ ወርሃዊና ሳምንታዊ የእምነት በዓላት ሲከናወኑ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ የዝግጅቱ ባለቤት በዕለቱና ወዲያው አካባቢውን ካላጸዳ፤ | ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 27 | የታክሲና ሚኒባስ ተራ አስከባሪ፤ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት፤ በጫማ ጥገናና ጽዳት (ሊስትሮ) የተሰማራ፤ በእረፍት ቀን (ቅዳሜና እሁድ) መንገድ ላይ የሚነግዱ ነጋዴ፤ ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የእንስሳት የግብይት ማዕከላት እና የመሳሰሉትን የሚሰራበትን አካባቢ እስከ 5 ሜትር ዙሪያ ከቆሻሻ ጽዱ ያላደረገ ማንኛውም ሰው፤ | ለግለሰብ ብር 2000.00<br>ለድርጅት ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ጽዳት |
| 28 | የባቡር ሀዲድ የተዘረጋባቸውን መስመሮችና የባቡር ፌርማታዎች ከደረቅ ቆሻሻ እንዲጸዳ ያላደረገ የቀላል ባቡር ድርጅት፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ከቆሻሻ ማጽዳት |
| 29 | የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የእምነት ተቋማት፤ ትምህርት ቤቶች፤ ንግድ ድርጅቶች፤ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሰራተኞቻቸውን አስተባብረው በጽዳት ንቅናቄው ተሳታፊ ያላደረገ ተቋም/ድርጅት፤<br>የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት በመኖሪያ አካባቢው በጽዳት ንቅናቄ ተሳታፊ ያልሆነ አባወራ ወይም እማወራ፤ | ብር 5,000.00<br>ብር 2000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና በንቅናቄ ተሳታፊ መሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 30 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት/ማህበር/ተቋም ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ሰራተኞቹ/አባላቱ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ሳይጠቀም አገልግሎት ከሰጠ ወይም ንጽህናውን ያልጠበቀ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ተጠቅሞ አገልግሎት ከሰጠ፤ | ብር 5,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንጹህ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት መጠቀም |

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 31 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ የጽዳት ድርጅት በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ያልተፈቀደ ደረቅ ቆሻሻ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም ማዕከል ወይም ወደ ማቃጠያ ማዕከላት አንጉዞ ካመጣ፤<br><br>ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ፈቃድ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውጪ ወደ ከተማው ያስገባ ማንኛውም ሰው፤<br><br>በመረብ ወይም በሸራ ያልተሸፈነ ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ ጭኖ ወደ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም ማዕከል ወይም ማቃጠያ ማዕከላት አንጉዞ ያመጣ ድርጅት /ማህበር/ ግለሰብ/ ተቋም፤ | ብር 50,000.00<br><br>ብር 100,000.00<br><br>ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻውን ወደ መጣበት ቦታ መመለስ |
| 32 | ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመደበበት የስራ ቦታ ወይም ምደባ ውጭ ደረቅ ቆሻሻ ከሰበሰበ፤ | ብር 50,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |
| 33 | ሰራተኞች በቸልተኝነት ወይም ሆን ብለው በመንገድ ዳር የተተከሉ አትክልት ውሃ ሲያጠጡ አፈር ወደ መንገዱ እንዲወጣ እና መንገድ እንዲቆሸሽ ያደረጉ፤ | ብር 5000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |

Lawyer.et When Results Count.

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 34 | አንድ ተቋም/ድርጅት ከውሀ መውረጃ ቱቦ የተጠረገ ቆሻሻ ከመንገድ ዳር እስከ 2 ቀን ካላነሳ | ብር 20000 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 35 | ማንኛውም ሰው ለግንባታ መከለያ በታጠረ አጥር ወይም በሕንጻ አጥር ላይ ስዕል የሳለ ወይም ጽሁፍ የጻፈ፣ ማስታወቂያ ወይም ጽሁፍ የለጠፈ፣ ያንጠለጠለ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በስልክ ምሶሶ፣ በድልድይ ስር ምሶሶ፤ በአፈር መደገፊያ ግንብ፣ ለግንባታ መከለያ በታጠረ አጥር፣ በሕንጻ አጥር ላይ ማስታወቂያ ወይም ጽሁፍ የለጠፈ | ለግለሰብ ብር 2000<br>ለድርጅት ብር 25000 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |
| 36 | መኪና ባልተፈቀደ ቦታ በማጠብ ወይም በማሳጠብ አካባቢው እንዲቆሸሽ ያደረገ ማንኛውም ሰው፤ | ያጠበ ብር 2000.00<br>ያሳጠበ ብር 20,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣትና አካባቢውን ማጽዳት |

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

When Results Count.